# የ“አቦል” መፅሐፍ ግብዣ

ዳንኤል አበራ <danlinet@yahoo.com>

በቶሮንቶ ኪነ ጥበብ አፍቃሪያን የተቋቋመው “ሐዲስ ንጋት የኪነ ጥበብ መድረክ” አባላትና ወዳጆች ለኢትዮጵያ 2000 ኢ.ም. 11 መጣጥፍ እና 57 ግጥም በ220 ገጽ አካትተው፣ ዋጋውንም በሃያ ዶላር ተምነው፣ ርእሱንም “አቦል” አሰኝተው ለንባብ አብቅተዋል።

የታደሙ ግብዣ ጥሪያቸውም ይህን ይመስላል። “የክረምት አመዳይ ሲወርድብን፤ የበጋ ፀሃይ ሲቆላን፤ የመጸው ቁር ሲያበራየን ወደ ራሳችን ተመልሰን፤ ልባችንን ከፍተን፤ ጸደይን እንፈልጋለን። ውቅያኖስ ተሻግረን “ኢዮሃ አበባዬን!” እናዜማለን። የማዕበሉን ስልት ለመከተል እንሞክራለን - “silent night…” እያልን። እናም የተለያዩ ዓለማትን ደቁሰን ዘላለማዊ ውበት ለመፍጠር ስንዳክር እንኖራለን። ውበትን ፍለጋ ከጭላሎ እስከ ሂማሊያ በምናባችን እንባዝናለን። ከተራራው ጦስኙን፤ ከጓሮ ጤናዳሙን፤ ከሜዳ ሃሪቲውን፤ ከዓባይ ጨኸቱን፤ ከአመዳይ ንጣቱን፤ ከጨው ጣዕሙን፤ ከሰው ክፋቱን፤ ጥፋቱን፤ ልማቱን፤ ከሁሉም በላይ ፍቅሩን፤ ቀላቅለን፣ ጨምቀን፣ ብእራችንን ሞልተን ወረቀታችን ላይ አንጠባጥበናል። በልባችሁ ኮለል ብሎ እንዲወርድ ጥረናል።” የሐዲስ ንጋት ወዳጆቻችን በማሳረጊያቸውም “ተሳክቶልን ይሆን?” ብለው አንባቢን ጠይቀዋል።

ከመጽሃፉን በጦማር ባጭር ጊዜ ውስጥ ከመላክ አንስቶ የኔ የአንዱ አንባቢ መልስ “አዎን” ተሳክቶላችኋል። ምርቃቴም በአቦል እንደ ጀመራችሁ በቶናና በበረካውም እንገናኝ ነው።
መጽሃፉ ሲላክልኝ ጠይቄ እንደተረዳሁት ለኢትዮጵያ 2000 እንዲደርስላቸው ጥድፊያ ከመኖሩና አንዳንድ የአርትኦት ስራ ግድፈት ከመታየቱ በስተቀር ከሞላ ጎደል አፍን ሞልቶ ጥሩ ስራ ነው ለማለት እደፍራለሁ።

እስኪ ስለ አቦል አንዳንድ ወግ እንሰልቅ። ከኪነ ጥበብ ተዋጽኦ በተጨማሪ ሲጀመር ከመጽሃፉ ሁልአቀፍ ዲዛይን አንስቶ የ5 አርታኢያን እና የ24 ደራሲያንን ተሳትፎ በ11 መጣጥፍ እና 57 ግጥም ያካተተ ስራ ነው። ይህን ስል ግን 29 የተለያዩ ሰዎች ናቸው ለማለት እንዳልሆነ ልብ ይባልልኝ።

በዚህ በምእራቡ አለም አይደለም 21 ሰዎችን አሰባስቦ እንዲህ ያለ ስራ መስራት በአንድ ጎጆ ጥላ ስር የሚኖሩ ባልና ሚስት እኩል የመገናኛ ጊዜያቸውን ለማስተካከል ወራትን አመት መድከም ይጠይቃል።ይህ እንግዲህ ሐዲስ ንጋት “አቦል”ን ለማሳተም ሲያስብ ከእቅዱ ጀምሮ በጅሮንዱን አካቶ ከማተሚያ ቤት

ተመላላሹን እና ከህትመትም በኋላ ስርጭቱን የሚከታተሉ ሁሉ ድምር ጥረት ነው። ይህ ስብስብ በራሱ ለውዳሴ በቂ ነው።

ይህም ሆኖ በማንኛውም የኪነ ጥበብ መስፈርት “አቦል” የተሳካለት ነው ለማለት እደፍራለሁ። በዚህ የመነሻ ጽሁፌ ዝርዝር ትንተና ውስጥ ገብቼ አላሰለቻችሁም ግን አጠር አጠር አድርጌ በወፍ በረር እይታ መጽሃፉን አሳውቃችኋለሁ።

ስለ አስራ አንዱ መጣጥፍ

የሐዲስ ንጋቶቹ አክሊሉ ረዳ “ነመስቴ”ን እና የ“ልቤ ድምጽ”ን፤ ባዩ በየነ  “ቤተሰብ” እና “ያንድ ሌሊት ጎጆ”ን፤ ወፈፌ “የሠራዊት እጆች” እና “ቀጠሮ”ን፤ ጴጥሮስ ደጀኔ “ጎብኚው” እና “የምርቃት ቆብ”ን ሲያቀርቡ ዮሴፍ ያእቆብ ደግሞ “ትንሣኤ”ን “አንዳንድ ቀንማ...”ን እና “የሁለት ዓለም ሰው”ን አቅርበዋል።

ስለ ሀምሳ ሰባቱ  ግጥም

አስራ ዘጠኙ ሐዲስ ንጋቶች እያንዳንዳቸው ከአንድ እስከ ስምንት ግጥሞችን ደርድረዋል። በዝርዝርም፦ ፈንታው አባተ (8) “ልቤን የሚያረካው”፣ “ለመቀነስ ተስማማሁኝ”፣ “የካርድ ሙሾ”፣ “የዓባይ ለቅሶ”፣ “ተስፋ አትቆርጥም”፣ “የኔ አስጋሪ”፣ “ለምን?” እና “ባለፈረሱን”፤ ጴጥሮስ ደጀኔ (5) “ግራ ገባኝ”፣ “የአፍ ፍቅር”፣ “ወለል ወይስ ጣሪያ”፣ “ደስታዬ” እና “እውነት ከሞት አፋፍ”ን፤ ባዩ በየነ (4) “ኢጋምና ቁልቋል”፣ “አባታችን ሆይ”፣ “ፍቅር ወይስ ቂጣ” እና “አበሳሽን እኖራለሁ”ን፤ ወፈፌ (4) “ፍለጋ”፣ “ያበሻ ቀጠሮ!”፣ “አለማቀፋዊ ወዛደራዊነት” እና “ኑሮ ከሁለት ተንጠልጥሎ”ን፤ ታምራት ገበየሁ (4) “ማር ከስኳር”፣ “አሸን ክረምት አግቢ”፣ “የማስቸግራችሁ” እና “የቀልድ ሰፍነግ”ን፤ ጸዳለ ታደሰ (4) “ላንቃ”፣ “ስደት”፣ “ጥርስ እና አጥንት” እና “ጥቋቁር ሠዓቶች”ን፤ ፋናዬ ድጋፌ (3) “ምስጋና”፣ “አንቺ ኢትዮጵያዊ ሴት” እና “ግሪሣን ባረገኝ”ን፤ ፋሲካ ወ/ሰንበት (3) “ይቅርታ”፣ “ልጅነቴ” እና “ቅንነት እና ሰቀቀን”ን፤ ቴዎድሮስ ደስዬ (3) “ተዉ አትፍረዱብኝ”፣ “በከራ” እና “ሆስፒታል ቢጤ”ን፤ወንድወሰን ኃይሉ (3) “ማን ስቆ ጀመረ”፣ “ሰባቂ ዕምባዎች” እና “ጥላ ልሁን ባልከ”ን፤ ዮሀንስ አያሌው (3) “ህሊና”፣ “ቤቴን” እና “ዐፄ ሳዳም”ን፤ አሰፋ ወ/ሩፋኤል (2) “ቢሆንም” እና “ገሎ ማዳን”ን፤ ሂሩት ዳኛቸው (2) “ዕምባዎቼ” እና፣ “ነፍሳት”ን፤ ሮዚና ገሥሠው (2) “ንቢት” እና “የስልክ ካርድ”ን፤ ዮሐንስ ታደሰ (2) “እንጥፉ” እና “የጨው ኑሮ”ን፤ ዮሴፍ ያዕቆብ - ጌራ (2) “ከሞተ ቆይቷል” እና “ነፍስ”ን ሲያቀርቡ ሶስቱ ገጣሚያን ዓለማየሁ አስፋው፣ ዕዮብ ከበደ እና ሕይወት አምባቸው እያንዳንዳቸው አንዳንድ ግጥም “ወርቀ ዘቦ”ን፣ “የልቤ በረኛ”ን፣ እና “ሲቀር ሲቀር”ን አቅርበዋል።

ሐዲስ ንጋቶች በ“አቦል” ወፌ ቆመች ብለዋል። በቶናና በረካቸው ደግሞ እንደሚሄዱና እና እንደሚሮጡ እንጠብቃለን። የከርሞ ሰው ይበለን!